# የመሰረታዊ ለውጥ ዋስትናችን

# ብሄራዊ መግባባትን እውን በማድረግ ብቻ የሚገኝ ነው !

ከአክሊሉ ወንድአፈረው

**(ethioandenet@bell.net )**

ኦገስት **14፣2018**

ዶክተር አብይ የሚመሩት የለውጥ ሀይል በህዝብ ግፊት ወደ ስልጣን ከመጣ ካለፉት አራት ወራት ወዲህ እጅግ ብዙ አስደሳችና ተስፋ ሰጭ ተግባሮችና ጅምሮችን እየተመለከትን ነው። ሰብአዊ መብት በመከበር ላይ ነው ፣ በፖለቲካ አመለካከት ምክንያት መታሰርና መገረፍ እየቀረ ነው ፣ መጻፍ መናገር ወዘተ አያሳስርም፣ መደራጀት ይቻላል የፖለቲካ እስረኞች እየተፈቱ ነው ፣ መዳረሻቸው ያልታወቁትንም ማፈላለግ እንደሚቀጥል ቃል ተገብቷል፤ በስደት ላይ የነበሩና በመሳሪያ ትግል ይፋለሙ የነበሩ ሳይቀሩ ወደሀገር ተመልሰዋል ወይም በመመለስም ላይ ናቸው። ዛሬ በኢትዮጵያችን ይህ ሁሉ እጅግ አስደሳች ብቻ ሳይሆን ከ 27 አመቱ ህወሀት መራሹ አገዛዝ መዳከም ጋር ተያይዞ መሰረታዊ ለውጥ ለመጀመሩ ምልክት ነው።

የተጀመረው ለውጥ ወደፊት እንዲሄድና የዴሞክራሲ ስርአት መሰረት እንዲጥል ለማድረግ ደግሞ እስካሁን ከተጓዝንበት የበለጠ ርቀት መሄድ ይበልጥ የተወሳሰቡ ችግሮችን በድፍረት መፍታት ደረጃ በደረጃ ሁሉን አሳታፊ ስርአትን መገንባት የግድ ይላል።

የዴሞክራሲ መሰረት ጠንካራ ወይም ተወዳጅ ግለሰብ ሳይሆን ጠናካራ ተቋማት ሲሆኑ ትግሉ አስተማማኝና ቀጣይነትም ያለው ይሆናል።

ዶክተር አብይ ሲናገሩ እንደተሰማውም ዴሞክራሲን ለመገንባት ማበረታታት የሚያስፈልገው ሞጋች እንጂ እሽ ባይ ዜጋ አይደለም ። ይህ ደግሞ እውን እንዲሆን ይህን ሁኔታ የሚያበለጽግ መሰረት ማጣል ያሰፈልጋል። ዴሞክራሲ ብልጭ ብሎ ከታየ በኋላ ያንድ ሰሞን ግር ግር እንዲሆን ብቻ ሳይሆን በቀጣይነት እንዲያድግ የሚያሰችል ምህዳር መፋጠር ያሰፈልጋል።

እነዚህን ሁሉ ተ

ባራዊ ለማድረግ ደግሞ ሁሉም ባለድርሻወች የሚሳተፉበትና በሀገራችን ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ እስካሁን ከተዘፈቅንበት አጥፊ ስርአት ወደ ዴሞክራሲአዊ ስርአት ልንጓዝ የሚያሰችለን የጋራ እቅድ በሁሉም ባለድርሻወች ተሳትፎ መንደፍ ያሰፈልጋል። የምንሸጋገረው በምን መልክ በሚለው ላይ ባቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሽግግሩን ሂደት እውን ለማድረግስ ምን መቸ በማን መሰራት እንዳለበት በጋራ መወሰንና መግባባት ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው።

ይህ ሲሆን ሁሉም ባለድርሻ፤ ሁሉም ዜጋ ስርአቱን የኔ ነው የሀገሩንም ህግጋት መከበር አለባቸው ብሎ እንዲያምንና እንዲንከባከብ ሁኔታወች ይመቻቻሉ።

ሁላችንም እንደምናውቀው ላለፉት 27 አመታት በስልጣን ላይ የቆየውና የሀገራችን መሰረታዊ ችግሮች ዋና ምንጭ የነበረው ኢህአዴግና የኢህአዴግ ፖሊሲወች ናቸው። ዛሬ ከኢህአዴግ የወጡ የለውጥ ሀይሎች እነ ዶክተር አብይን እንደግፍ ስንል እሁንም ኢህአዴግ የጥፋቱ ባለቤት የመፍትሄውም ብቸኛ ባለቤት ሆኖ ሁሉንም ጠቅልሎ ይዞ ወደ ዴሞክራሲ ሊያሸጋግረን ይችላል ለማለት አይደለም።

ይህ ሊሆን አይችልም፤ አገዛዙም ስርአቱም ለ 27 አመታት ከቆየበት አጣብቂኝና ይከተለው ከነበረው አጥፊ ርእዮት እንዲህ በቀላሉ ሊጸዳ አይችልም። አገዛዙ አቅፈው ደግፈው ያቆዩት ተቋማቱ፣ ባለስልጣኖችና ተጠቃሚዎች ሁሉ፣ ሁሉንም ነገር ድንገት እርግፍ አድርገው የለውጥ ሀይል ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህም ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የማሸጋገሩን ሀላፊነት በብቸኝነት ኢህአዴግ ሊሸከም ከቶውንም አይችልም፡፡

ከዚህ አዙሪት ለመውጣት ያለው እንዱና ዋናው አማራጭ ብሄራዊ መግባባትን እውን የሚያደርግ ብሄራዊ ጉባኤ ባስቸኳይ መጥራትና በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለምሳሌም በምርጫ ህጉ፤ በምርጫ ቦርዱ አወቃቀርና በመጭው ምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ በፖለቲካ ፖርቲወች ህግ ላይ የጸጥታ ሀይሉንና ሰራዊቱን ገለልተኛ በማድረግ ላይ፣ በየቦታው የሚታዩ ግጭቶችን በማብረድና በማስቆም ላይ፣ በዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ ላይ፣ የፍትህ ስርአቱን ነጻና ገለልተኛ በማድረግ ላይ ወዘተ መግባባትና የጋራ በይነ እቅድ (ሮድ ማፕ) ማውጣት ያሰፈልጋል። አንዳንዶቹ አጀንዳወች ባጭር ጎዜ ሌሎች ደግሞ ረዘም ባለ ጊዜ መፈታት እንደሚገባቸው የታወቀ ሲሆን ይህን የጊዜ ሰሌዳም ሆነ ሂደቱን በተመለከተም ቢሆን የባለድርሻወች ተሳትፎና የውሳኔው ባለቤቶች መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው።

ብዚ ጊዜ እጅግ የተካረረ (የተቋሰለ) ፖለቲካ ስር በሰደደበት ሀገር እና ባጠቃላይም ከአምባገነን ስርአት ወደ ዴሞክራሲ በሚደረግ ሽግግር ትልቁ ተግዳሮት በተለያዩ ባለድርሻወች መሀል መግባባትን መፍጠር አለመቻል ነው። ብሄራዊ መግባባት የሚለው ቃል ሲነሳ ብዙወችን የሚያሰጨንቃቸው ይህ ጉዳይ ነው።

በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በቀላሉ ስምምነትን እውን ማድረግ ቀላል አለመሆኑ ራሱ ሀገራችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋጋጥ ይህን አስቸጋሪ ጉዞ መጓዝና ተግዳሮቱንም መወጣት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል።

በተለያዩ ሀገሮች ወደ ዴሞክራሲ የተደረገ ሽግግር ልምድ እንደሚያሳየን በዚህ ሂደት ውስጥ እጅግ ቀልጣፋ ውጤትን ለማግኘት በሁሉም ባይሆን በአብዛኛው ባለድርሻዎች ተደማጭነትና አክብሮት ያለው መሪ መኖር እጅግ ቁልፍ ጉዳይ ነው። የደቡብ አፍሪካን የዘረኞች መንግስት ወደዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር በተደረገው ሂደት ታላቅ ሚና የተጫወቱት በተለያዩ ባለድርሻወች ታላቅ ተቀባይነትና ክብር የነበራቸው ታላቁ መሪ ኔልሰን ማንዴላ ነበሩ።

በሀገራችንም ውስጥ ዶክተር አብይ ዛሬ በብዙ ባለድርሻወች ዘንድ እጅግ ታላቅ አክብሮችንና ታአማኒነትን አግኝተዋል። በመሆኑም ይኸን ተቀባይነት ( የፖለቲካ ካፒታል) በመጠቀም ዶክተር አብይና የለውጥ ሀይሉ ለብሄራዊ መግባባት እውን መሆን ታላቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚያስችላቸው ልዩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። ይህን ተግባር ብሄራዊ ጉባኤውን ባስቸኳይ በመጥራት፣ባለድርሻወች በተወሰነ ጊዜ ወደ ጋራ መግባባት እንዲደርሱ በማበረታታት ተጽእኖ በማድረግና በመሳሰሉት እጅግ ሊያግዙና አመራር ሊሰጡበትም ይችላሉ። ዶክተር አብይና የለውጥ ሀይሉ ብቃቱም ተቀባይነቱም ስላላቸውም ታላቅ ውጤታማነት ያለው ስራ ባጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ አንዲሆን ሊያደርጉ ይችላሉ።

ይህ ሲሆን አሁን በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ በከፍተኛ ደረጃ በህዝብ የታቀፈ ፣ ሰፊ ተቋማዊ መሰረት ያለው እንዲሆን ስለሚያደርግ በቀላሉ የማይናጋ ቀጣይነቱም ይበልጥ አስተማማኝ እንዲሆን ማድረግ ይችላል።

ብሄራዊ መግባባት ሲኖር ሁሉም ባለድርሻ የራሱን አሻራ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ስለሚያይ ስርአቱን የኔ ብሎ ለመቀበልና የወደፊት ግጭቶችንም ለማስወገድ ታላቅ መሰረት ይጥላል፤፡ ለሀገር እንድነትም አስተማማኝ መሰረት ይሆናል።

ይህ ሂደት ለዴሞክራሲ ስርአት

ንባታም እጅግ ጠንካራ መሰረት የሆኑ ህግጋትና ተቋማት መሰረት መጣል ብቻ ሳይሆን በጊዜ ሰሌዳ የተደገፈ በማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ ፣ ሁሉም የተስማማበት ተጨባጭ ሽግግር ሂደት እንዲኖር ያስችላል።

ከውጭ ለሚመለከቱ ሁሉም የሀገራችን የለውጥ ሂደት በአስተማማኝ መሰረት ላይ የሚገነባ እንጂ በተወሰኑ ክፍሎች በጎ ፈቃድ ላይ የተንጠለጠለ እንዳልሆነ ስለሚያመላክት የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንትን ይጋብዛል የቅርብና የሩቅ ወዳጆቻችንም በሀገራችን ላይ ያላቸውንም መተማመን ያጠነክራል።

እንደሚባለውም ለነጻነት መታገልን ያልመረጡ ሁሉ ነጻነትን ሊያጡ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም በመሆኑ አሁን በትግላችን እውን የሆነውንና እያጣጣምነው የሚገኘውን ለውጥ ስር እንዲሰድና እንዳለፉት ጊዜያት እንዳይነጠቅ ለማድረግ ብሄራዊ መግባባትን እውን ለማድረግ ለሚያስችለው ታላቅ የዘመናችን ሀገራዊ ፕሮጀክት ተግባራዊ መሆኑ ያለአንዳች ማመንታት ሁላችንም መረባረብ ይኖርብናል።

በዚህ ረገድ ይህን ታላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት ተግባራዊ እንዲሆን በማመቻቸት ዶክተር አብይም ሆኑ ባስተዳደሩ ውስጥና ካስተዳደሩ ውጭ የሚገኙ የለውጥ ሀይሎች በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ታሪክ ሰርተው ታላቅ ውለታን ለሀገራችንና ለህዝባችን ማበርከት የሚችሉበት ሌላ እድል አሁንም ከፊት ለፊታችን ይገኛል። ጥያቄው ይህን ሀላፊነት ባግባቡ እንወጣዋለን ወይንስ ዳግም እናባክነዋለን የሚለው ነው።